




# በ Washington ግዛት ውስጥ የቅድመ ጣልቃ ገብነት አገልግሎቶች

## የቤተሰብ መመሪያ

*Individuals with Disabilities Education Act (የአካል ጉዳተኞች የትምህርት ሕግ፣ IDEA)*


Washington State Department of
CHILDREN, YOUTH & FAMILIES



ልጅዎ መዘግየቱን ሲያውቁ ብዙ ስሜቶች ሊኖሩዎት ይችላሉ። ፍርሃት ሊሰማዎት ይችላል፣ የተነገረውን ነገር ላያምኑ ይችላሉ ወይም ደግሞ ቁጣ ሊሰማዎት ይችላል። እነዚህ ያልተለመዱ ስሜትዎች ናቸው፣ እናም እርስዎ ብቻዎን አይደሉም። ሌሎች ወላጆችም እንደዚው እነዚህን ልምዶች እና ስሜትዎች አላቸው። እነዚህ ስሜቶች ወይም ስጋቶች ካጋጠሟቸው ሌሎች ወላጆች ጋር እንዲገናኙ የሚያግዙዎት ክልል አቀፍ ፕሮግራሞች አሉ። ለበለጠ መረጃ እና እርዳታ በዚህ መጽሐፍ ጀርባ ላይ የተዘረዘሩትን የወላጅ ድጋፍ ቁጥሮች መደወል ይችላሉ።

## ዉድ ወላጆች፣

*ይህንን ቡክሌት ካለዎት ምናልባት የልጅዎ እድገት ስጋት እንዳለብዎ ወይም ልጅዎ የእድገት መዘግየት እንዳለበት እንደተነገረዎት አውቃለሁ።*

*ሴት ልጄ ሱዚ ለእድገቷ መዘግየቶች በፈተና ውስጥ ስትሆን ምን ያህል እንደተደናገጥኩ እና ግራ እንደተጋባሁ አስታውሳለሁ። እንዴት አገልግሎት ማግኘት እንዳለብኝ ይቅርና ባለሙያዎች የሚጠቀሙባቸውን ብዙ ቃላቶች እራሱ አልገቡኝም።*

*አንዴ አገልግሎቱን በብዙ አጋዥ አስተማሪዎች እና ቴራፒስቶች በኩል ካገኘን በኋላ፣ የእርሷ እድገት በእርግጥ ተሻሽሏል። በእነዚያ አስጨናቂ የመጀመሪያዎቹ ዓመታት ባደረገችው የመጀመሪያ ጣልቃ ገብነት ምክንያት፣ ዛሬ ባለችበት ቦታ በጣም አመስጋኝ ነኝ። እንዲሁም፣ ከሌሎች ወላጆች ጋር መገናኘት እና መረጃን መጋራት ለቤተሰባችን በጣም አስፈላጊ ነገር ነበር።*

*ይህንን ቡክሌት ለአገልግሎቶቹ እንደ መመሪያ እንደሚጠቅም እና የቤተሰብዎን ፍላጎቶች እንደሚደግፉ ተስፋ አደርጋለሁ።*

**Cassie፣ ወላጅ**

# ይዘቶች


መግቢያ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 2

ቅድመ ጣልቃ ገብነት ምንድን ነው? . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 3

ስለ ልጄ እድገት ጥያቄ ቢኖረኝስ ምን ማድረግ እችላለው? . . . . . . 4

በWashington ውስጥ ለቅድመ ጣልቃ ገብነት ብቁ
የሆነው ማነው? . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 5

ቀጣይ ላይ ምንድን ነው የሚፈጠረው? . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 6

እድሜያቸው 3 ሲሆን ምንድን ነው የሚፈጠረው? . . . . . . . . . . . . 7

Individuals with Disabilities Education Act ( የአካል
ጉዳተኞች የትምህርት ሕግ፣ IDEA) ስር ያሉኝ መብቶች
ምንድ ናቸው? (የአሠራር መከላከያዎች) . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 8


የልጄን ወይም የቤተሰቤን አገልግሎቶችን በሚመለከት
ውሳኔ ካልተስማማውስ? . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 10

እገዛ ስፈልግ ወይም ተጨማሪ መረጃ ስፈልግ ከየት
ማግኘት እችላለው? . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 11

እኔ እንዴት እየበለጠ ተሳታፊ መሆን እችላለው? . . . . . . . . . . . . . 12

ያ ማለት ምን ማለት ነው? (መዝገበ ቃላት). . . . . . . . . . . . . . . . . .13

እውቅናዎች . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 14

# መግቢያ

*“ልጄ በስድስት ወሩ አሁኑም መነሳት አይችልም ነበር። ምናልባት የሆነ ስህተት እየሰራሁ እንደሆነ እንዳስብ አረገኝ። ከቅድመ ጣልቃ ገብነት ፕሮግራም ጋር እንድገናኝ ወደ ረዳኝ ሀኪማችን(ዶክተር) ወሰድኩት። አሁን ልጄ በጣም ጠቃሚ የሆኑ አገልግሎቶችን እያገኘ ይገኛል። ጥሩ ለውጥ እያሳየ ነው፣ እና ምን ማድረግ እንደምችል የበለጠ እየተማርኩ ነው። Ian ነገሮችን እንደሌሎች ልጆች በፍጥነት ያላደረገው ስህተት እየሰራሁ ስለነበር እንዳልሆነ አሁን አውቃለሁ።”*

***Heather፣ ወላጅ***



**የዚህ መመሪያ ዋና አላማ** እርስዎ እና ቤተሰብዎ የ Washington ግዛት Department of Children, Youth, and Families (የህጻናት፣ ወጣቶች እና ቤተሰቦች ዲፓርትመንት፣ DCYF) Early Support for Infants and Toddlers (ቅድመ ድጋፍ ለጨቅላ ህጻናት እና ታዳጊዎች፣ ESIT) ፕሮግራም አጠቃላይ እይታን መስጠት ነው። በESIT ፕሮግራም ውስጥ የቤተሰብዎ ተሳትፎ በእርስዎ ምርጫ ነው። ልጅዎ ለESIT ፕሮግራም ቅድመ ጣልቃ ገብነት አገልግሎት ብቁ ሆኖ ከተገኘ የልጅዎ እድገት መዘግየቶችን ለመፍታት ለልጅዎ እና ለቤተሰብዎ ይገኛሉ።

ይህ መመሪያ ስለ ስቴት አቀፍ የESIT ፕሮግራም አጠቃላይ እና ጠቃሚ የሆኑ መረጃ ይሰጥዎታል፣ እንደ ወላጅ ያሉዎትን አንዳንድ መብቶች ዝርዝር ጨምሮ። ለእርስዎ እና ለቤተሰብዎ ስላሉት የሥርዓት ጥበቃዎች/የወላጅ መብቶች የተሟላ እና የበለጠ ዝርዝር መግለጫ “Individuals with Disabilities Education Act (የአካል ጉዳተኞች የትምህርት ሕግ፣ IDEA) ክፍል ሐ የሥርዓት ጥበቃዎች (የወላጅ መብቶች)” በሚባል የተለየ ሰነድ ቀርቧል። ይህንን መመሪያ ስታነቡ፣ የ family resources coordinator (የቤተሰብ ሀብቶች አስተባባሪ፣ FRC) ወይም ከESIT ፕሮግራም የመጣ ሰው ስለ ፕሮግራሙ ሊኖርህ የሚችለውን ማንኛውንም ጥያቄ ሊመልስ ይችላል።

በዚህ ሰነድ ውስጥ፣ ለቅድመ ጣልቃገብነት ብዙ የተለመዱ ቃላት ጥቅም ላይ ይውላሉ። ስለ አንዳቸውም ጥያቄዎች ካሉዎት እና ትርጓሜ ከፈለጉ፣ የቃላቶቹን መዝገበ ቃላት ለማግኘት ወደዚህ ቡክሌት ገጽ 13 ያዙሩ።

## የWashington ክልል Early Support for Infants and Toddlers (ቅድመ ድጋፍ ለጨቅላ ህጻናት እና ታዳጊዎች፣ ESIT)

እንደ ወላጅ፣ እርስዎ በልጅዎ ሕይወት ውስጥ በጣም አስፈላጊ ሰዎች ነዎት። በመጀመሪያዎቹ ሶስት አመታት ውስጥ ልጆች በፍጥነት ያድጋሉ እንዲሁም ይለወጣሉ። ስለ ልጆችዎ እንዲሁም እንዴት እያደገ/እያደገች እንደሆነ ያስቡ። ልጅዎን በደምብ ያውቃሉ። ልጅዎ ፈገግ ሲል፣ ሲቀመጥ፣ ሲራመድ፣ ሲያወራ ወይም መጠጫ ነገር ሲይዝ የመሳሰሉ ነገሮችን ያስተውሉ። አሁን እያዩት ያለው ንገር ልጅዎ በተለያዩ የእድገት ደረጃዎች ውስጥ እንዴት እያደገ እንደሆነ ነው። አንድ ልጅ በእድገት ላይ መዘግየት ሲኖረው ፣ የሚያስፈልጉት አገልግሎቶች በሁሉም ግዛቶች ይገኛሉ። የWashington ስቴት Early Support for Infants and Toddlers (ቅድመ ድጋፍ ለጨቅላ ህጻናት እና ታዳጊዎች፣ ESIT) ፕሮግራም ቤተሰቦች እነዚህን አገልግሎቶች እንዲያገኙ የግዛት አቀፍ ጥረትን ያስተባብራል።

# ቅድመ ጣልቃ ገብነት ምንድን ነው?

የቅድመ ጣልቃ ገብነት አገልግሎቶች በሕዝብ ቁጥጥር እና በተፈጥሮ አካባቢዎች የሚሰጡ የልማት አገልግሎቶች ናቸው። ብቁ የሆኑ ጨቅላዎችን ወይም ታዳጊዎችን የዕድገት ፍላጎቶች ለማሟላት የተነደፉ ናቸው እና ወላጆች ልጃቸውን እንዲያድግ እና እንዲማር ለመርዳት የተነደፉ ወይም ዲዛይን የተደርጉ ናቸው።

ቅድመ ጣልቃ ገብነት (በልጅ ህይወት የመጀመሪያ አመታት) እርስዎን በመርዳት ትልቅ ለውጥ ሊያመጣ ይችላል፦

- ለልጅዎ የሚፈልጉትን አገልግሎቶች ይፈልጉላቸው።
- የልጅዎን የብልጽና እድገት ይረዱ።
- የልጅዎን ትምህርት እና እድገት እንዲሁም በቤት እና በማህበረሰብ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ስኬታማ ተሳትፎን ይደግፉ።

## የቅድመ ጣልቃ ገብነት ዓላማ ምንድን ነው?

የቅድመ ጣልቃ ገብነት አላማ በእድገት መዘግየት እና የአካል ጉዳት ያለባቸውን ልጆች በዕለት ተዕለት የመማር እድሎች እድገት ለማሳደግ ቅንጅቶችን፣ ድጋፎችን፣ ግብዓቶችን እንዲሁም አገልግሎቶችን በመስጠት በቤተሰብ ጥንካሬዎች ላይ መገንባት ነው።

ቤተሰቦች ልጃቸውን እንዲንከባከቡ እና በቤተሰብ እና በማህበረሰብ እንቅስቃሴዎች እንዲሳተፉ ለማስቻል፣ ቤተሰቦች የሚከተሉትን ነገሮች ያደርጋሉ፦

- መብቶቻቸውን ይወቁ።
- የልጆቻቸውን ፍላጎቶች በደምብ ያነጋግሩ።
- ልጃቸው እንዲያድግ እና እንዲማር ያግዙ።

ልጆች በተለያዩ ሁኔታዎች እና ሁኔታዎች ንቁ እና ስኬታማ ተሳታፊዎች እንዲሆኑ ለመርዳት ልጆች የሚከተሉትን ያሳያሉ:-

- አዎንታዊ ማህበራዊ-ስሜታዊ ክህሎቶች እና ማህበራዊ ግንኙነቶች።
- ቋንቋ እና ግንኙነትን ጨምሮ እውቀትን እና ክህሎቶችን ማግኘት እና መጠቀምን ማዳበር።
- ፍላጎታቸውን ለማሟላት ተገቢ ባህሪያትን አጠቃቀም።



## Individuals with Disabilities Education Act (የአካል ጉዳተኞች የትምህርት ሕግ፣ IDEA) ምንድን ነው?

በ1986 ኮንግረስ Individuals with Disabilities Education Act (የአካል ጉዳተኞች የትምህርት ሕግ፣ IDEA) በመባል የሚታወቀውን ህግ አሻሽሏል እና ክልሎች ለአካል ጉዳተኛ ልጆች እና ለቤተሰቦቻቸው የቅድመ ጣልቃ ገብነት አገልግሎቶችን በክልል አቀፍ ደረጃ እንዲገነቡ እና እንዲተገብሩ የሚያበረታታ ፕሮግራም ፈጥሯል። ሕጉ ጨቅላ ሕፃናት እና ታዳጊዎች አካል ጉዳተኛ ለሆኑ ቤተሰቦች, አገልግሎት ለመስጠት እስቴቶች(ግዛቶች) ሊከተሏቸው የሚገቡ መስፈርቶችን አዘጋጅቷል። እያንዳንዱ ግዛት በ IDEA በተገለጸው መሰረት የቅድመ ጣልቃ ገብነት አገልግሎቶችን መስጠቱን መቀጠል ይችል እንደሆነ በየዓመቱ ዉሳኔውን ይሰጣል። Department of Children, Youth, and Families (የህጻናት፣ ወጣቶች እና ቤተሰቦች ዲፓርትመንት፣ DCYF) Early Support for Infants and Toddlers (ቅድመ ድጋፍ ለጨቅላ ህጻናት እና ታዳጊዎች፣ ESIT) ፕሮግራም የቅድሚያ ጣልቃ ገብነት አገልግሎቶችን የግዛት አቀፍ ሥርዓት ቅንጅትን ይመራል።

የቅድመ ጣልቃ ገብነት አገልግሎቶች የእያንዳንዱን ብቁ ልጅ የእድገት ፍላጎቶች እና የልጁን እድገት ከማጎልበት ጋር የተያያዙ የቤተሰብ ፍላጎቶችን ለማሟላት የተነደፉ ናቸው።

የምልክት ቋንቋ አስተርጓሚ ከፈለጉ አንዱ ሊቀርብልዎ ይገባል። እንግሊዘኛ መናገር የማይችሉ ከሆነ፣ ግልጽ ለማድረግ የማይቻል ካልሆነ በስተቀር አስተርጓሚ ሊሰጥዎ ይገባል።

# ስለ ልጄ እድገት ጥያቄ ቢኖረኝስ ምን ማድረግ እችላለው?

በአካባቢዎ የሚገኘውን የመሪ family resources coordinator (የቤተሰብ ሀብቶች አስተባባሪ፣ FRC) ጋር ይደውሉ። FRC ዎች በእያንዳንዱ ካዎንቲ ወይም አካባቢዎች ውስጥ ይገኛሉ። ድርሻቸው ልጅዎ ሊያስፈልጋቸው የሚችላቸውን የቅድመ ጣልቃገብነት አገልግሎቶችን እንዲያገኙ ማገዝ ነው። የአከባቢዎን አመራር FRC ስም ለማወቅ Family Health Hotline (የቤተሰብ ጤና የስልክ መስመር ቁጥር) በ1-800-322-2588 ላይ ይደውሉ። እንዲሁም ለአካባቢው የጤና መምርያ ወይም የትምህርት ቤት ዲስትሪክት መደወል ይችላሉ።

ስለ ስጋትዎ ከጤና እንክብካቤ አቅራቢዎ ጋር ያውሩ። እሱ/እሷ ማጣሪያ ማቅረብ ወይም ሌሎች ግብዓቶችን ሊጠቁሙ ይችላሉ። ዶክተር ከሌልዎት እና ተጨማሪ መረጃ ወይም እርዳታ ከፈለጉ፣ ከላይ ወደተጠቀሰው Family Health Hotline (የቤተሰብ ጤና የስልክ መስመር ቁጥር) ይደውሉ። ወደ ቅድመ ጣልቃ ገብነት አገልግሎቶች ለመግባት የዶክተር ሪፈራል አያስፈልግዎትም። እንደ ወላጅ እራስዎን በራስዎ ሪፌር ማድረግ ይችላሉ።

## ማጣራት(እስክሪኒንግ) ምንድን ነው?

የማጣሪያ ምርመራ ልጅዎ እንዴት እንደሚማር እና እንደሚያድግ በፍጥነት መቃኘት ማለት ነው። የማጣሪያ ምርመራው ልጅዎ እንዴት እያደገ እንደሆነ ለማወቅ በሰለጠኑ ሰዎች ነው የሚከናወነው። የልጅዎ እድገት አሳሳቢ ከሆነ FRCዎ ለልጅዎ ግምገማ እንዴት ማግኘት እንደሚችሉ መረጃን ሊያካፍል ይችላል።



## ግምገማ ምንድን ነው?

ግምገማ ብልጅዎ እድገት ላይ ጥልቅ የሆነ እይታን ይሰጣል። ግምገማው የሚደረገው ከእርስዎ፣ ከልጅዎ እና ከቅድመ ጣልቃ ገብነት ባለሙያዎች ጋር ነው።

ግምገማው እነዚህን የእድገት ዘርፎች ይመለከታል፡-

- የእውቀት (ኮግኒቲቭ)– የመማር ችሎታ እና ልጅዎ እንዴት እንደሚማር ነው
- አካላዊ– የመንቀሳቀስ፣ የማየት እና የመስማት ችሎታ
- ተግባቦት– ቋንቋን የመረዳት እና ፍላጎቶችን የመግለፅ ችሎታ ነው
- ማህበራዊ ወይም ስሜታዊ – ከሌሎች ጋር የመዛመድ ችሎታ
- የመላማድ ክህሎቶች – እራሱን ወይም እራሷን የመልበስ, የመብላት እና የመንከባከብ ችሎታ ነው።

ግምገማ ልጅዎ ለቅድመ ጣልቃገብነት አገልግሎት ብቁ መሆኑን የምናረጋግጥበት መንገድ ነው። ግምገማው የሚከናወነው በእርስዎ የጽሁፍ ፈቃድ ብቻ ነው እናም ከእርስዎ ምንም አይነት አይጠበቅብዎትም።

የግምገማ እቅድ አወጣጥን ለመገምገም ያሉ ጠቃሚ ምክሮች፡-

- የተለያዩ family resources coordinator (የቤተሰብ ሀብቶች አስተባባሪ፣ FRC) ለማግኘት ይጠይቁ።
- ስለልጅዎ እድገት ሊኖርዎት የሚችሉትን ማንኛውንም ጥያቄዎች ወይም ስጋቶች ይዘው ይምጡ።
- አስፈላጊ ነው ብለው ያሰቡትን መረጃ ሁሉ ያካፍሉ:- እንደ የህክምና መዛግብት፣ የህፃን መጽሐፍ፣ የእድገት ገበታ ወይም ሌሎች ሪፖርቶች።
- ለእርስዎ እና ለቤተሰብዎ ምን ጊዜዎች ወይም አካባቢዎች እንደሚሻል ዉሳኔዎን ይስጡ።
- ከፈለጉ ሌሎች የቤተሰብ አባላትን፣ ጓደኛዎን ወይም ድጋፍ ሰጪ ሰውን ይጋብዙ።
- ማንኛውም አስተርጓሚ ወይም ሌላ እርዳታ ከፈለጉ FRC ዎን ያሳውቁ።

ከግምገማው በኋላ እርስዎ እና ሌሎች የቡድኑ አባላት ልጅዎ ስለሚያደርገው ነገር ይነጋገራሉ እና ስጋቶችን ይለያሉ። የመዘግየት ቦታዎች ካሉ ልጅዎ ለቅድመ ጣልቃ ገብነት አገልግሎቶች ብቁ ሊሆን ይችላል። እነዚህን አገልግሎቶች ለመቀበል ወይም ላለመቀበል ምርጫ አለህ።

# በWashington ውስጥ ለቅድመ ጣልቃ ገብነት ብቁ የሚሆነው ማነው?

ብቁ ለመሆን አንድ ልጅ 25 በመቶ መዘግየት ወይም 1.5 standard deviation(ስታንዳርድ ዲቪኤሽን) ከእድሜው በታች በሆነ አንድ ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ የእድገት ቦታዎች ማሳየት አለበት። አንድ ልጅ እንደ ዳውን ሲንድሮም ያለ አካላዊ ወይም አእምሯዊ ሁኔታ ካለበት፣ ይህም የእድገት መዘግየትን ያስከትላል።

## ምዘና(ግምገማ) ምንድን ነው?

ምዘና ከእርስዎ፣ ከሌሎች ልጅዎን ከሚያውቁት እና የቅድመ ጣልቃ-ገብ አቅራቢዎች የልጅዎን ባህሪ እና እድገት በብዙ የተለመዱ ልማዶች እና እንቅስቃሴዎች ለመረዳት ሊጠቀሙበት ከሚችሉት ሂደቶች የመረጃ ስብስብ ነው። ምዘና(ግምገማ) ልጅዎ ከሌሎች ጋር እንዴት እንደሚገናኝ እና ምን እንደሚወደው እንዲሁም የሚያበሳጭ ወይም የሚከብድባቸውን አዳዲስ ክህሎቶችን እንዴት እንደሚማር ይመለከታል። የግምገማው መረጃ እርስዎ እና ቡድንዎ በምን አይነት ውጤቶች(ለውጦች) መስራት እንደሚፈልጉ እና እነዚያን ውጤቶች ለማሳካት የሚያግዙ አገልግሎቶችን እና ድጋፎችን እንዲወስኑ ይረዳዎታል።

እንዲሁም ግምገማው ልጅዎን ወደ ውጤት ለማምጣት የሚያደርገውን እድገት ለመወሰን እና የሚያገኙዋቸው አገልግሎቶች እና ድጋፎች ልጅዎ እድገት እንዲያደርግ እየረዱት መሆኑን ለማረጋገጥ ጥቅም ላይ የሚውሉ ቀጣይ ሂደቶችን በውስጡ ያካትታል።



# ቀጥሎ ምን ይፈጠራል?

## Individualized Family Service Plan (ግላዊ የቤተሰብ አገልግሎት እቅድ፣ IFSP)

ብቁ ከሆኑ፣ ልጅዎ የ IDEA ቅድመ ጣልቃ ገብነት አገልግሎቶችን ሊቀበል ይችላል። Family resources coordinator (የቤተሰብ ሀብቶች አስተባባሪ፣ FRC) እና ከሌሎች አገልግሎት አቅራቢዎች ጋር ስብሰባ ይኖርዎታል። የእርስዎ ቤተሰብ፣ ከሌሎች ጋር፣ የ Individualized Family Service Plan (ግላዊ የቤተሰብ አገልግሎት እቅድ፣ IFSP) የተባለ ዕቅድ ይጽፋሉ። ዕቅዱ የቤተሰብዎን ስጋቶች፣ ፍላጎቶች እና እሴቶች የሚያንፀባርቅ መሆኑን ለማረጋገጥ ከ FRC ዎ ጋር በመሆን ይስሩ።

አገልግሎቶቹ ከIFSP ጋር እና ለአገልግሎቶቹ ሲስማሙ ነው የሚጀምሩት።

IFSP የልጅዎን እና የቤተሰብዎን ተለዋዋጭ ፍላጎቶች የሚያሟላ ቀጣይ ሂደት ነው። ቢያንስ በየስድስት ወሩ ይገመገማል እንዲሁም በየዓመቱ እንደ አዲስ ይጻፋል።



IFSP የሚከተሉትን ያካትታል፡-

- **የአሁኑ ደረጃ ተግባር ድረጃዎች** – ልጅዎ አሁን ምን እየሰራ ነው።
- **የቤተሰብ መግለጫ** – የቤተሰብዎ ስጋትዎች፣ ቅድሚያ የሚሰጧቸው ነገሮች እና ሀብቶች መግለጫ፤ የቤተሰብ መግለጫዎ የIFSP አስፈላጊ አካል ነው፣ ነገር ግን ከሌለዎት መምረጥ ይችላሉ።
- **ዉጤቶች** – ለልጅዎ እና ለቤተሰብዎ ሊያዩዋቸው የሚፈልጓቸው ለውጦች።
- **የቅድመ ጣልቃ ገብነት አገልግሎቶች የሚፈለጉት** – ለምን ያህል ጊዜ እና ለምን ያህል ጊዜ፣ የት እንደሚሆኑ እና ማን እንደሚከፍላቸው (ብዙ የተለያዩ ምንጮች የቅድመ ጣልቃ ገብነት አገልግሎቶችን ይደግፋሉ)። በቅድመ ጣልቃ ገብነት ፕሮግራም ውስጥ እየተሳተፉ ከሆነ፣ የሚሰጣችሁን ማንኛውንም አገልግሎት መቀበል ወይም አለመቀበል ይችላሉ(ከቤተሰብ ሀብቶች ማስተባበር በስተቀር)።
- **የተፈጥሮ አካባቢዎች** – የቅድመ ጣልቃገብነት አገልግሎቶች የሚቀርቡበት የተፈጥሮ አካባቢ መግለጫ ነው። በተፈጥሮ አካባቢዎች አገልግሎት የማይሰጥ ከሆነ፣ IFSPs የጽሁፍ ማረጋገጫ ማካተት አለባቸው።
- **የጊዜ መስመርዎች(ታይምላይንስ)** – አገልግሎቶች መቼ እንደሚጀምሩ እና እንደሚያልቁ እና እቅድዎን እንደገና የሚመለከቱበት ጊዜ።
- **በ IDEA መሠረት የገንዘብ ድጋፍ የሌላቸው ሌሎች የሚያስፈልጉ አገልግሎቶች** - እነዚህን አገልግሎቶች ለማግኘት ማን ሊረዳዎ ይሚችል።
- **Family resources coordinator (የቤተሰብ ሀብቶች አስተባባሪ፣ FRC)** – በእቅድዎ ውስጥ ተሰይሟል.
- **ከ 3 ዓመቱ በፊት የሚወጣ የሽግግር እቅድ** – ልጅዎ 3 ዓመት ከሆነው በኋላ አገልግሎቶችን መፈለግ እና ማቀድ።

ምናልባት ሌሎች የቤተሰብ አባላትን፣ ጓደኛዎን ወይም ደጋፊዎን ወደ ስብሰባው መጋበዝ ይፈልጉ ይሆናል። ስለ ልጅዎ በጣም አስፈላጊ ነው ብለው የሚያምኑትን ማንኛውንም መረጃ ያምጡ።

# እድሜያቸው 3 ሲሆን ምንድን ነው የሚፈጠረው?

ልጅዎ 3 ዓመት ከመሆናቸው በፊት ቢያንስ ከስድስት እስከ ዘጠኝ ወራት በፊት family resources coordinator (የቤተሰብ ሀብቶች አስተባባሪ፣ FRC) ወደ ቀጣዩ አገልግሎት ሰጪ ወይም ልጅዎን የሚያገለግል ኤጀንሲ ለመዘዋወር ለማቀድ ያግዝዎታል። ይህ አገልግሎት የት እና እንዴት እንደሚሰጥ ሊቀይር ይችላል። በቅድመ ጣልቃ ገብነት ውስጥ፣ ይህ ለውጥ ሽግግር ይባላል። IDEA ለዚህ ሽግግር ጹፋዊ የሆነ እቅድ ይፈልጋል። የሽግግር እቅድ ስብሰባ ልጅዎ 3 ዓመት ሳይሞላው ቢያንስ ከ90 ቀናት በፊት መከናወን አለበት። የሽግግር እቅድዎ ልጅዎ ሊያስፈልጋቸው የሚችላቸውን ልዩ ትምህርት ወይም ማህበረሰብ አቀፍ አገልግሎቶችን ይለያል።

የሽግግር እቅድ ለማውጣት ቀጣዩ ኤጀንሲ ወይም አገልግሎት አቅራቢ ማግኘት እንዲችል የእርስዎ FRC የፍቃድ ቅጽ እንዲፈርሙ ይጠይቅዎታል። በእርስዎ፣ በእርስዎ FRC፣ አገልግሎት ሰጪ(ዎች) እና በአካባቢው የትምህርት ቤት ዲስትሪክት መካከል ስብሰባ ይዘጋጃል።

የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት ልጅዎ ለቅድመ ትምህርት ቤት ልዩ ትምህርት አገልግሎት ብቁ መሆኑን ይወስናል። የፈተናዎቻቸውን ውጤት ከእርስዎ ጋር ይወያያሉ እና ስለመብቶችዎ መረጃ ይሰጡዎታል። ልጅዎ ብቁ ከሆነ አገልግሎታቸው በ Individualized Education Program (ግለሰባዊ የትምህርት ፕሮግራም, IEP) በኩል ይሰጣል።

ልጅዎ ለልዩ ትምህርት ቅድመ ትምህርት ቤት አገልግሎት ብቁ ካልሆነ፣ የእርስዎ FRC ወደ ሌሎች ሊሆኑ የሚችሉ አገልግሎቶች ለመዘዋወር ለማቀድ ይረዳዎታል።

### ስል ሽግግር ስብሰባው ያሉ ጠቃሚ ምክሮች፡-

- ስለታቀደው ለውጥ በተቻለ መጠን ብዙ መረጃ ይሰብስቡ።
- ሊኖሩ ስለሚችሉ የፕሮግራም አማራጮች ወይም ምርጫዎች ይጠይቁ።
- አዲሱ ፕሮግራም ለቤተሰቦች ምን አይነት ስልጠና እና ድጋፍ እንደሚሰጥ ይጠይቁ።
- ከለውጡ በፊት አዲሱን ፕሮግራም ይጎብኙ።
- የጽሁፍ ቁሳቁሶችን ይጠይቁ እና ወደ አዲሱ ፕሮግራም ለመግባት እና ለመሳተፍ ያሉትን ሂደቶችን ይወቁ።
- ስለ ልጅዎ በተቻለ መጠን ብዙ መረጃ ለአዲሱ ፕሮግራም ይስጡ።



# በIndividuals with Disabilities Education Act (የአካል ጉዳተኞች የትምህርት ሕግ፣ IDEA) ስር ያሉኝ መብቶች ምንድ ናቸው?

*(የአሠራር መከላከያዎች)*

አብዛኛዎቹ ህጎች የዜጎችን መብቶች በውስጣቸው የሚያካትቱ ሲሆኑ IDEAም ከዚህ የተለየ አይደለም። የእርስዎ  family resources coordinator (የቤተሰብ ሀብቶች አስተባባሪ፣ FRC) መብቶችዎን የሚያብራራውን "Individuals with Disabilities Education Act (የአካል ጉዳተኞች የትምህርት ሕግ፣ IDEA) ክፍል ሐ የሥርዓት ጥበቃዎች (የወላጅ መብቶች)ን" ይሰጥዎታል።

## በ IDEA ስር ያሉ የመብቶችዎa ምሳሌዎች የሚከተሉትን የማግኘት መብትዎን ያካትታሉ:-

- ለልጅዎ ዋና እና የመጨረሻ ውሳኔ ሰጪ የመሆን መብትዎ።
- የሚከተሉትን የሚያካትቱ አገልግሎቶችን ማግኘት፡-
  - ስጋቶችን አስቀድሞ መለየት/ድጋፍ የሚሻን ልጅ መለየት
  - ወቅታዊ ሁለገብ ግምገማ እና ምዘና
  - የልጅዎ ብቁነት ዉሳኔ አስጣጥ
  - የቤተሰብ ሀብቶች አስተባባሪ/ ማስተባበር

## ልጅዎ ብቁ ከሆነ የሚከተሉትን ማድረግ አለብዎት፡-

- Individualized Family Service Plan (ግላዊ የቤተሰብ አገልግሎት እቅድ፣ IFSP)።
- እስከ የልጅዎ ሶስተኛ ልደት ድረስ ከFRC ጋር በመካሄድ ላይ ያለ የቤተሰብ ሃብት ማስተባበር።
- የተለያ የfamily resources coordinator (የቤተሰብ ሀብቶች አስተባባሪ፣ FRC) ን ለማግኘት ይጠይቁ።
- ከልጅዎ እድገት ጋር የተያያዙ የቅድመ ጣልቃገብነት አገልግሎቶችን ይቀበሉ።
- በIFSP ሂደት እንደተወሰነው ልጅዎ እና ቤተሰብዎ የሚያገኟቸውን አገልግሎቶች መቀበል ወይም አለመቀበል።
- በIFSP ቡድን የሚመከሩ አንዳንድ አገልግሎቶችን ውድቅ ያድርጉ እና አሁንም ሌሎች አገልግሎቶችን (ከFRC አገልግሎቶች በስተቀር) ያግኙ።
- የልጅዎን የቅድመ ጣልቃ ገብነት አገልግሎቶች እና የአገልግሎቶች አሰጣጥ ለውጦችን በሚመለከቱ በሁሉም ስብሰባዎች ላይ ይሳተፉ።
- ለቤተሰብዎ ተስማሚ በሆነ ጊዜ እና ቦታ ስብሰባ ያድርጉ።
- በአፍ መፍቻ ቋንቋዎ ወይም በቤትዎ ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውለው የመገናኛ መንገድ ማስታወቂያዎችን እና የIFSP ሰነዶችን ይውሰዱ።





## እንዲሁም የልጅዎን ቅድመ ጣልቃገብነት መዝገቦች በተመለከተ መከላከያዎች አሉዎት። ይህም የሚከተሉትን የማድረግ ማብትዎን ያካትታሉ፦

- መዝገቦችን ይገምግሙ እንዲሁም በመዝገቦቹ ላይ ማሻሻያዎችን ይጠይቁ።
- የሰነዶቹን ግልባጮች ይውሰዱ።
- ፕሮግራሙ ውስጥ የተሰበሰቡ፣ የሚያዙ ወይም የሚገለገሉባቸው መዝገቦች ዓይነቶች እና ቦታዎች እነማን በፕሮግራሙ ውስጥ እነዚያን መዝገቦች ማግኘት እንደሚችሉ እንዲሁም እነዚህን መዝገቦች መቼ እንደሚያዩ ይወቁ።
- የመዝገቦቹን ሪከርዶች ወይም ቅጂዎችን ማን እንዳየ ለማወቅ መረጃ ይጠይቁ።
- ትክክል አይደለም ወይም አሳሳች ወይም የልጅዎን ወይም የቤተሰብዎን ግላዊነት ወይም መብት ይጥሳል ብለው ባመኑበት መዝገብ ውስጥ ያለ መረጃ ይመርምሩ። የልጅዎ የቅድሚያ ጣልቃገብነት መዝገቦች ከሚከተሉት ነገሮች መካከል ያካትታሉ:-
  - የማጣርያ ሪፖርቶች
  - የግምገማ ሪፖርቶች
  - የምዘና መረጃ
  - የብቁነት ዉሳኔ
  - የ IFSP አካል የሆኑ ሁሉንም መረጃዎች

## ስለ ቤተሰብዎ ያለው መረጃ ሚስጥራዊ ነው። የሚከተሉትን የማድረግ መብቶች አሏቹ፦

- የሚከተሉትን ጨምሮ የግል እና ሊለዩ የሚችሉ መረጃዎች ምስጢራዊነት፦
  - የልጅዎ፣ የእራስዎ ወይም የሌላ የቤተሰብ አባላት ስም።
  - የልጅዎ አድራሻ።
  - ምክንያታዊ በሆነ እርግጠኝነት ልጅዎን ለመለየት የሚያስችሉት የግል ባህሪዎች ዝርዝር ወይም ሌሎች መረጃዎች።
- ሚስጥራዊነት እንዴት እንደሚጠበቅ የአካባቢ ፖሊሲዎችን እና ሂደቶችን ይጠይቁ።
- መረጃን ወይም መዝገቦችን ለመለዋወጥ ወይም ለማጋራት በመረጃ የተደገፈ የጽሁፍ ፈቃድ ይስጡ።

ከወላጅ/ቤተሰብ መብቶች በተጨማሪ ልጆች የሚከተሉት ነገሮች ከሆኑ ምትክ ወላጅ የማግኘት መብት አላቸው፦

- ምንም ወላጅ ሊታወቅ የማይችል ከሆነ።
- የአገልግሎት አቅራቢው/የሕዝብ ኤጀንሲ ከተመጣጣኝ ጥረት በኋላ ወላጅ ያሉበትን ቦታ ማወቅ አይችልም።
- ልጁ በግዛቱ ከለላ ውስጥ ነው።



# የልጄን ወይም የቤተሰቤን አገልግሎቶችን በሚመለከት ውሳኔ ካልተስማማውስ?

ስለ ችግሩ እባክዎን ከfamily resources coordinator (የቤተሰብ ሀብቶች አስተባባሪ፣ FRC) ጋር ይነጋገሩ። ያ የማይሰራ ከሆነ ወይም ካልተመችዎት ከሚከተሉት አማራጮች አንዱን ወይም ሁሉንም ለመጠቀም መምረጥ ይችላሉ፡-

- **ሽምግልና** – አለመግባባቶችን ለመፍታት ለማገዝ ሽምግልና ያለ ምንም ወጪ ይቀርብልዎታል። ሽምግልና ወይም ማስታረቅ ከመደበኛ የአስተዳደር ችሎት እንደ አማራጭ ቀርቧል። ሽምግልና የበፈቃደኝነት ሂደት ነው።
- **የጥብቅና አገልግሎቶች** – እነዚህ መረጃዎችን የሚሰጡ እና ችግሩን እንዴት መፍታት እንደሚችሉ ለማቀድ የሚረዱ ፕሮግራሞች ናቸው። አንዱ የጥብቅና አገልግሎት ሰጪ ተቋም PAVE ነው(ገጽ 11 ይመልከቱ)። የእርስዎ FRC በአካባቢዎ ስላለው የጥብቅና አገልግሎት መረጃ ሊሰጥዎ ይችላል።
- **የፍትህ ሂደት ችሎት (በመቀጠል)** – ይህ በአስተዳደር ችሎት መኮንን የሚመራ መደበኛ ችሎት ወይም ሂደት ነው። የአስተዳደር ችሎት ጥያቄ በጽሁፍ መሆን አለበት እንዲሁም ቅሬታውን በውስጡ ማካተት አለበት። ጥያቄውን ለቅድመ ጣልቃ ገብነት አገልግሎት አቅራቢው ዳይሬክተር ወይም ለአካባቢዎ የቅድመ ጣልቃ ገብነት አገልግሎት ተቋራጭ ያቅርቡ። የእርስዎ FRC ስማቸውን እና አድራሻቸውን ሊሰጥዎ ይችላል ወይም ደግሞ **esit@dcyf.wa.gov** ኢሜይል መላክ እና እርዳታ መጠየቅ ይችላሉ።

ማንኛውም ወላጅ፣ ሌላ ሰው ወይም ድርጅት ኤጀንሲ ወይም የቅድመ ጣልቃ ገብነት አገልግሎት አቅራቢ የህግ መስፈርት እየጣሰ ነው ብለው ካሰቡ አስተዳደራዊ ቅሬታ ሊያቀርቡ ይችላሉ። ቅሬታው መፃፍ፣ መፈረም እንዲሁም ስለ ቅሬታው እውነታዎችን በውስጡ ማካተት አለበት።

ቅሬታውን ወደ ሚከተሉት ይላኩ፡-

**Early Support for Infants and Toddlers (ቅድመ ድጋፍ ለጨቅላ ህጻናት እና ታዳጊዎች) Department of Children, Youth, and Families (የህጻናት፣ ወጣቶች እና ቤተሰቦች ዲፓርትመንት)**
PO Box 40970
Olympia, WA 98504-0970

ቅሬታው ይገመገማል እንዲሁም ምላሹ በ60 ቀናት ውስጥ ይፃፋል።



# እገዛ ስፈልግ ወይም ተጨማሪ መረጃ ስፈልግ ከየት ማግኘት እችላለው?

የሚከተሉት ድርጅቶች እና ቡድኖች ተጨማሪ መረጃ፣ እርዳታ እና ድጋፍ ሊሰጡ ይችላሉ፦

### Family Health Hotline (የቤተሰብ ጤና የስልክ መስመር ቁጥር)

1-800-322-2588

**www.withinreachwa.org**

ይህ የጥሪ መስመር Family Resources Coordinators (የቤተሰብ ሀብቶች አስተባባሪ፣ FRCs) ጨምሮ በህዝባዊ እና በግል የቅድመ ጣልቃ ገብነት ግብዓቶች ላይ ወቅታዊ መረጃን ይያዘ ነው። በተጨማሪም በWashington ስላሉት የክትባት፣ የአመጋገብ እና ሌሎች የህጻናት ጤና አገልግሎቶች መረጃን በዉስጡ የያዘ ነው።

---

### Department of Children, Youth, and Families (የህጻናት፣ ወጣቶች እና ቤተሰቦች ዲፓርትመንት፣ DCYF) Early Support for Infants and Toddlers (ቅድመ ድጋፍ ለጨቅላ ህጻናት እና ታዳጊዎች፣ ESIT) ፕሮግራም

ኢሜል፦ **esit@dcyf.wa.gov**

**www.dcyf.wa.gov**

የ IDEA ክፍል ሐ የቅድመ ጣልቃ ገብነት አገልግሎቶችን በክልል አቀፍ ደረጃ ይመራል።

---

### ወላጅ ለወላጅ

1-800-821-5927

**www.arcwa.org**

የአካል ጉዳተኛ ታዳጊ ልጆች ወይም የእድገት መዘግየቶች ያለባቸው ልጆች ላላቸው ወላጆች ስሜታዊ ድጋፍ እና መረጃ የሚሰጥ በስቴት አቀፍ የወላጅ መረብ ነው።

### የWashington ግዛት የአባቶች ኔትዎርክ

425-747-4004 ext. 218

**https://fathersnetwork.org**

ልዩ ፍላጎት ያላቸው ልጆች ላሏቸው ሁሉም ወንዶች እና ቤተሰቦቻቸው የጠበቃ እና ድጋፍ እና ግብዓቶችን ይሰጣል።

---

### Washington PAVE (Partnerships for Action, Voices for Empowerment (የድርጊት፣የማጎልበት ድምፆች ለመስጠት ያለ አጋርነት))

1-800-5PARENT

**wapave.org**

ክልል አቀፍ የአካል ጉዳተኛ ልጆች ላሏቸው ቤተሰቦች እርዳታ እየሰጠ ያለ የወላጅ ማሰልጠኛ እና የመረጃ ማዕከል ነው።



# እኔ እንዴት እየበለጠ ተሳታፊ መሆን እችላለው?


እርስዎ ለልጅዎ ፕሮግራሞችን እና አገልግሎቶችን በማቀድ እና በማዘጋጀት ረገድ ትልቅ ሚና አለዎት። እንዲሁም ማህበረሰብዎ እንዴት አገልግሎቶችን እንደሚሰጥ በማቀድ መሳተፍ ይችላሉ።

ይህ የእቅድ አወጣጥ በካውንቲ ደረጃ በ County Interagency Coordinating Councils (የካውንቲ መስተጋብራዊ አስተባባሪ ምክር ቤቶች፣ CICCs) በኩል ነው የሚከናወነው። እያንዳንዱ CICC ወላጆች በምክር ቤቱ አባልነት እንዲኖራቸው ይጠበቅባቸዋል። ከሁሉም አባላት ጋር፣ ወላጆች እንዴት አገልግሎቶች በተሻለ ሁኔታ እንደሚሰጡ ዉሳኔ ለመስጠት ይረዳሉ። የCICC ስብሰባዎች ለሕዝቡ ክፍት ናቸው።

እንዲሁም State Interagency Coordinating Council (የክልል ኤጀንሲ መስተጋብር አስተባባሪ ምክር ቤት፣ SICC) አለ። እንዲሁም ይህ ካዎንሲል የወላጅ ውክልናም ሊኖረው ይገባል። የSICC ስብሰባዎች ለሕዝቡ ክፍት ናቸው። ስለ መሰብሰቢያ ጊዜ እና ቦታ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት የቤተሰብ መርጃዎች አስተባባሪዎን (ESIT) ያነጋግሩ ወይም ድህረ ገጹን በ**www.dcyf.wa.gov**ን ይጎብኙ።

ይህ ቡክሌት የ Washington ስቴት Early Support for Infants and Toddlers (ቅድመ ድጋፍ ለጨቅላ ህጻናት እና ታዳጊዎች) ፕሮግራም ማጠቃለያ ነው። በ IDEA ስር በWashington በተፈቀደው እቅድ ላይ ሙሉ ዝርዝሮችን ወይም ስለ የእርስዎ CICC ወይም SICC የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ በ **esit@dcyf.wa.gov** የ Washington ግዛት Early Support for Infants and Toddlers (ቅድመ ድጋፍ ለጨቅላ ህጻናት እና ታዳጊዎች) ፕሮግራምን ያነጋግሩ።

**www.dcyf.wa.gov**



# ያ ማለት ምን ማለት ነው? (መዝገበ ቃላት)

### አስተዳደራዊ ስሚ ችሎት

የወላጆች/ቤተሰብ እና የኤጀንሲዎች ማስረጃዎችን እና ክርክሮችን የሚያዳምጥ እና ማን ትክክል እንደሆነ እና ማን ምን ማድረግ እንዳለበት የሚወስን የችሎት መኮንን፣ ከገለልተኛ ሰው ጋር የሚደረግ መደበኛ ሂደት።

### ምዘና

በልጁ የቅድመ ጣልቃ ገብነት ልምድ ውስጥ ልዩ ፍላጎቶቹን ለመለየት ብቁ ባለሙያዎች የሚጠቀሙባቸው ቀጣይ ሂደቶች፤ የቤተሰቡ ሀብቶች፣ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ነገሮች እና ከእድገቱ ጋር የተያያዙ ስጋቶች፤ እና እነዚህን ፍላጎቶች ለማሟላት የሚያስፈልጉ የቅድመ ጣልቃ-ገብ አገልግሎቶች ተፈጥሮ እና መጠን።

### ድጋፍ ሰጪ የቴክኖሎጂ መሳሪያዎች

የልጅዎን ነገሮችን የመሥራት ችሎታ ለመጨመር፣ ለመጠገን ወይም ለማሻሻል የሚያገለግል ማንኛውም ዕቃ፣ ቁራጭ ወይም የምርት ሥርዓት (ለምሳሌ፡ መብላት፡ መግባባት፡ መንቀሳቀስ)።

### ድጋፍ ሰጪ የቴክኖሎጂ አገልግሎትዎች

ለአካል ጉዳተኛ ልጅ የሚሆን የረዳት ቴክኖሎጂ መሳሪያን ለመምረጥ፣ ለማግኘት ወይም ለመጠቀም በቀጥታ የሚረዳ አገልግሎት።

### የልጆች መፈለግያ

ቀደም ብሎ መለየትን፣ ማጣራት፣ ሪፈራል እና የመጀመሪያ አገልግሎት ማስተባበርን በውስጡ ያካትታል።

### ቅድመ ጣልቃ ገብነት

በመንግስት እና በግል ኤጀንሲዎች የሚሰጡ አገልግሎቶች ስብስብ እና ብቁ የሆኑ ልጆችን እና ቤተሰቦችን ለመደገፍ በህግ የተነደፉት ከልደት እስከ 3 አመት እድሜ ያለው ልጅ የእድገት እና የእድገት እምቅ ችሎታን ለማሳደግ ነው።

### ግምገማ

በሁሉም የእድገት በታዎች ላይ የሕፃኑን ወይም የሕፃኑን ሁኔታ በመወሰን ላይ ያተኮረ የልጁን የመጀመሪያ እና ቀጣይነት ለመወሰን ብቃት ባላቸው ባለሙያዎች የሚጠቀሙባቸው ሂደቶች፤ የእውቀት (ኮግኒቲቭ) ፤ ማህበራዊ / ስሜታዊ ፤ አካላዊ (ራዕይን እና መስማትን ጨምሮ) ፤ ግንኙነት እና መላመድ።

### ቤተሰብን ያማከለ እንክብካቤ

ወላጆችን እንደ ውሳኔ ሰጪነት የሚያስተዋውቅ እና የወላጅ/የሙያ አጋርነትን የሚገነባ መርህ።

### የወላጅ መግለጫ

በ Individualized Family Service Plan (ግላዊ የቤተሰብ አገልግሎት እቅድ፣ IFSP) ላይ የተካተቱ የቤተሰብ ጉዳዮች፣ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ነገሮች እና ግብዓቶች በቤተሰብ የሚመራ መግለጫ።

### Individualized Family Service Plan (ግላዊ የቤተሰብ አገልግሎት እቅድ፣ IFSP)

ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ብቁ ለሆኑ ልጆች እና ቤተሰቦች የቅድመ ጣልቃ ገብነት እና ሌሎች አገልግሎቶችን ለማቅረብ የጽሁፍ እቅድ:- (1) በቤተሰቡና በሚመለከታቸው ባለሙያዎች በጋራ የተዘጋጀ፤ (2) በልጁ እና በቤተሰቡ ሁለገብ ግምገማ እና ግምገማ ላይ የተመሰረተ፤ (3) ቤተሰቡ ከፈለገ የሀብት፣ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ጉዳዮች እና ጉዳዮች በቤተሰብ የሚመራ መግለጫ ያለው። እና (4) የልጁን እድገት ለማሳደግ አስፈላጊ የሆኑ አገልግሎቶችን እና የቤተሰቡን የእድገት ፍላጎቶችን ለማሟላት ያለውን አቅም የሚጨምር።

### አካል ጉዳተኛ የሆኑ ሕፃናት እና ታዳጊዎች

ከተወለዱ ጀምሮ እስከ 3 ዓመታቸው ላሉ ሕጻናት የቅድመ ጣልቃገብነት አገልግሎት ብቁ የሆኑት 1.5 መደበኛ ልዩነት ወይም ቢያንስ 25 በመቶ የእድገት መዘግየት እያጋጠማቸው ነው ከሚከተሉት ውስጥ በአንዱ ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ አካባቢዎች የግንዛቤ፣ የአካል፣ የመግባቢያ፣ ማህበራዊ/ስሜታዊ ወይም መላመድ; ወይም በምርመራ የተረጋገጠ የአካል ወይም የአዕምሮ ሁኔታ የእድገት መዘግየት የመፍጠር እድሉ ከፍተኛ ነው።

### ሽምግልና

የሰለጠነ፣ የማያዳላ ሰው ግጭት ውስጥ ያሉ ወገኖች ልዩነቶቻቸውን እንዲፈቱ እና ለሁሉም ወገኖች አጥጋቢ መፍትሄ እንዲያገኝ የሚረዳበት መደበኛ ያልሆነ ሂደት።

### ሁለገብ

የተቀናጁ እና የተቀናጁ አገልግሎቶችን ለማቅረብ የሁለት ወይም ከዚያ በላይ የትምህርት ዓይነቶች ወይም ሙያዎች ተሳትፎ፣ የግምገማ እና የግምገማ እንቅስቃሴዎችን እና የ IFSP እድገትን ጨምሮ።

### የተፈጥሮ አካባቢዎች

ምንም የአካል ጉዳት ለሌላቸው ለልጁ የዕድሜ እኩዮች ተፈጥሯዊ ወይም የተለመዱ ቅንብሮች(መቼቶች)። ይህም የቤት፣ ሰፈር ወይም የማህበረሰብ ቅንብሮችን በውስጡ ሊያካትት ይችላል።

### ዉጤቶች

በቅድመ ጣልቃ ገብነት አገልግሎቶች ምክንያት በልጅዎ ወይም በቤተሰብዎ ላይ ማየት የሚፈልጓቸው ለውጦች መግለጫዎች። እነዚህ መግለጫዎች የ IFSP ው ክፍል ናቸው።

### ማጣርያ

ተጨማሪ ግምገማ እንደሚያስፈልግ ለማየት ስለ ልጅዎ እድገት ፈጣን ቼክሊስት ወይም ዳሰሳ።

### ተተኪ አሳዳጊ

በውሳኔ አሰጣጥ ሂደት የልጁን መብት ለማስጠበቅ በወላጅ ወይም በህጋዊ ሞግዚት ምትክ እንዲሰራ በአካባቢው ወይም በግዛቱ ኤጀንሲ የተሾመ ግለሰብ።

### የሽግግር እቅድ

በ3 ዓመታቸው የቅድመ ጣልቃ ገብነት አገልግሎቶችን ሲለቁ ለልጅዎ የተዘጋጀው እቅድ ወይም ፕላን።

# እውቅናዎች

የቤተሰብ መመሪያዎች የስራ ቡድን State Interagency Coordinating Council (የክልል ኤጀንሲ መስተጋብር አስተባባሪ ምክር ቤት፣ SICC) ኮሚቴ ናቸው ይህንን ቡክሌት ያዘጋጁት።

ዓላማው የአካል ጉዳተኞች እና የአካል ጉዳተኛ ታዳጊዎች ወላጆች በ Individuals with Disabilities Education Act (የአካል ጉዳተኞች የትምህርት ሕግ፣ IDEA) ስር የቅድመ ጣልቃ ገብነት አገልግሎቶችን እንዲረዱ ለመርዳት ነው።



የኮሚቴው አባላት ለዚህ መመሪያ ዝግጅት ላሳለፉት ሰዓታት ምስጋናችን ከልብ ነው:-

**Donna White, ሊቀመንበር**

Department of Health (የጤና መምሪያ)፣ የእናቶች እና የህጻናት ጤና

**Catherine Davis**

Us–Qwed–Eeth, Puyallup ዝርያ
ከውልደት እስከ ስድስት ያለ ፕሮጄክት

**Heather Hebdon**

Specialized Training of Military Parents (የወታደር ወላጆች ልዩ ሥልጠና፣ STOMP) ፕሮጀክት

**Kathy Hormann**

የልጆች የእድገት ማዕከል፣ ሱምነር

**Cassie Johnston**

Washington PAVE,
የወላጅ ተሳትፎ አስተባባሪ

**Lynne Leeper**

Washington PAVE, የወላጅ ስልጠና ፕሮጄክት

**Melanie Stafford**

Us–Qwed–Eeth, Puyallup ዝርያ
ከውልደት እስከ ስድስት ያለ ፕሮጄክት

**Kathy Blodgett፣ የቢሮ ሰራተኛ**

Department of Social and Health Services (የማህበራዊ እና የጤና አገልግሎቶች ዲፓርትመንት)፣ የቀድሞ የዋሽንግተን ስቴት የጨቅላ ህፃናት ቅድመ ጣልቃ ገብነት ፕሮግራም

**Barbie Faubion፣ የቢሮ ሰራተኛ**


Department of Social and Health Services (የማህበራዊ እና የጤና አገልግሎቶች ዲፓርትመንት)፣ የቀድሞ የዋሽንግተን ስቴት የጨቅላ ህፃናት ቅድመ ጣልቃ ገብነት ፕሮግራም

---

የሚከተሉትን ጨምሮ ሃሳባቸውን ላካፈሉ ሌሎች ወላጆች እና ባለሙያዎች እናመሰግናለን፡-

**Rita Dickey, Linda Gil, Terri Larson, Kathy Lollar, Julie Martino, Kathie Moudy, Joni Strong, Diana Sandoval እና Debbie Yanak.**

ቡክሌቶቹ ለWashington መመሪያ ሞዴል ሆነው ለማገልገል ለMaryland እና Pennsylvania ግዛቶች ልዩ እውቅና።





*DCYF ለሁሉም ለፕሮግራሞቹ እና አገልግሎቶቹ ዘር፣ ቀለም፣ ጾታ፣ ሃይማኖት፣ እምነት፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ የዜግነት ሁኔታ፣ የጾታዊ ዝንባሌ፣ እድሜ፣ የውትድርና ሁኔታ፣ ወይም የምንም አይነት አካላዊ፣ ስሜታዊ፣ ወይም የአዕምሮ እክልን በማየት አያዳላም እንዲሁም እኩል ተደራሽነትን ያቀርባል።*

*የዚህን እትም ነጻ ቅጂዎች በአማራጭ ቅርጸት ወይም ቋንቋ ማግኘት ከፈለጉ፣ እባክዎን የ DCYF Constituent Relations (የ DCYF የመሰብሰቢያ ግንኙነቶችን) በ 1-800-723-4831 ወይም በኢሜል **communications@dcyf.wa.gov** ያግኙ።*

DCYF PUBLICATION FS_0002 | DEL 11-005 AM (07-2023) Ahmaric